የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፳፭
አዲስ አበባ ጥር ፲፪ ቀን ፪ሺ፯

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

21st Year No. 25
ADDIS ABABA, 20th January 2015

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፫፻፴፭ /፪ሺ፯ ዓ.ም

የቃፍታ ሽራሮ ብሔራዊ ፓርክን መሰየሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ.......................................ገጽ ፯ሺ፱፻፺፱

አባሪ.......................................................ገጽ ፰ሺ፲፫

## CONTENTS

Regulation No. 335 /2014

Qafta Shiraro National Park Designation Council of Ministers Regulation .............................................Page 7999

Annex.........................................Page 8013

### የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፴፭/፪ሺ፯

### የቃፍታ ሽራሮ ብሔራዊ ፓርክን ለመሰየም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፪ አንቀጽ ፭ እና በዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር ፭፻፵፩/፲፱፻፺፱ አንቀጽ ፬(፪) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የቃፍታ ሽራሮ ብሔራዊ ፓርክን መሰየሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፴፭ /፪ሺ፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፣

፩/ "አዋጅ" ማለት የዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር ፭፻፵፩/፲፱፻፺፱ ነው፤

### COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 335 /2014

### COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE DESIGNATION OF THE QAFTA SHIRARO NATIONAL PARK

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definitions of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 and Article 4(2) of the Development, Conservation and Utilization of Wildlife Proclamation No. 541/2007.

**1. Short Title**

This Regulation may be cited as the "Qafta Shiraro National Park Designation Council of Ministers Regulation No.335 /2014".

**2. Definition**

In this Regulation unless the context otherwise requires:

1/ "Proclamation" means the Wildlife Development, Conservation and Utilization Proclamation No. 541/2007;

፬/ ከዚያም ሽሮና ጫፍ ላይ በ14 ዲግሪ 14 ደቂቃ 06 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ36 ዲግሪ 44 ደቂቃ 20 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አራት ድረስ፤

፭/ ከዚያም በ14 ዲግሪ 15 ደቂቃ 49 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ36 ዲግሪ 45 ደቂቃ 51 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አምስት ድረስ፤

፮/ ከዚያም በ14 ዲግሪ 15 ደቂቃ 27 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ36 ዲግሪ 46 ደቂቃ 24 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ስድስት ድረስ፤

፯/ ከዚያም እንደፊታውራሪ አካባቢ በ14 ዲግሪ 14 ደቂቃ 53 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ36 ዲግሪ 46 ደቂቃ 33 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሰባት ድረስ፤

፰/ ከዚያም በ14 ዲግሪ 14 ደቂቃ 02 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ36 ዲግሪ 49 ደቂቃ 32 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ስምንት ድረስ፤

፱/ ከዚያም በ14 ዲግሪ 13 ደቂቃ 39 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ36 ዲግሪ 50 ደቂቃ 38 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ዘጠኝ ድረስ፤

፲/ ከዚያም በ14 ዲግሪ 11 ደቂቃ 57 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ36 ዲግሪ 51 ደቂቃ 28 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አሥር ድረስ፤

፲፩/ ከዚያም በ14 ዲግሪ 11 ደቂቃ 31 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ36 ዲግሪ 50 ደቂቃ 55 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አሥራ አንድ ድረስ፤

4/ thence, up to beacon number 4 at the tip of Shirona at 14 degree 14 minutes 06 seconds latitude north and 36 degree 44 minutes 20 seconds longitude east;

5/ thence, up to beacon number 5 at 14 degree 15 minutes 49 seconds latitude north and 36 degree 45 minutes 51 seconds longitude east;

6/ thence, up to beacon number 6 at 14 degree 15 minutes 27 seconds latitude north and 36 degree 46 minutes 24 seconds longitude east;

7/ thence, up to beacon number 7 at 14 degree 14 minutes 53 seconds latitude north and 36 degree 46 minutes 33 seconds longitude east at around Ende Fitawrari;

8/ thence, up to beacon number 8 at 14 degree 14 minutes 02 seconds latitude north and 36 degree 49 minutes 32 seconds longitude east;

9/ thence, up to beacon number 9 at 14 degree 13 minutes 39 seconds latitude north and 36 degree 50 minutes 38 seconds longitude east;

10/ thence, up to beacon number 10 at 14 degree 11 minutes 57 seconds latitude north and 36 degree 51 minutes 28 seconds longitude east;

11/ thence, up to beacon number 11 at 14 degree 11 minutes 31 seconds latitude north and 36 degree 50 minutes 55 seconds longitude east;

፲፪/ ከዚያም በጎብለል ስካውት ማረፊያ ቤት አካባቢ በ14 ዲግሪ 10 ደቂቃ 32 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ36 ዲግሪ 52 ደቂቃ 31 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አሥራ ሁለት ድረስ፤

፲፫/ ከዚያም እንዳጭዑ በሚባለው ቦታ ላይ በ14 ዲግሪ 09 ደቂቃ 58 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ36 ዲግሪ 54 ደቂቃ 13 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አሥራ ሦስት ድረስ፤

፲፬/ ከዚያም ሀገረሰላም አካባቢ በ14 ዲግሪ 09 ደቂቃ 43 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ36 ዲግሪ 55 ደቂቃ 12 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አሥራ አራት ድረስ፤

፲፭/ ከዚያም ዓፅሚ ሐርማዝ በሚባለው ቦታ ላይ በ14 ዲግሪ 09 ደቂቃ 25 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ36 ዲግሪ 55 ደቂቃ 19 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አሥራ አምስት ድረስ፤

፲፮/ ከዚያም በ14 ዲግሪ 09 ደቂቃ 38 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ36 ዲግሪ 56 ደቂቃ 12 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አሥራ ስድስት ድረስ፤

፲፯/ ከዚያም በ14 ዲግሪ 09 ደቂቃ 46 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ36 ዲግሪ 58 ደቂቃ 02 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አሥራ ሰባት ድረስ፤

፲፰/ ከዚያም በ14 ዲግሪ 09 ደቂቃ 46 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ36 ዲግሪ 58 ደቂቃ 14 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አሥራ ስምንት ድረስ፤

፲፱/ ከዚያም በ14 ዲግሪ 09 ደቂቃ 41 ሴኮንድ

12/ thence, up to beacon number 12 at 14 degree 10 minutes 32 seconds latitude north and 36 degree 52 minutes 31 seconds longitude east at around the Goblel Scout Center;

13/ thence, up to beacon number 13 at 14 degree 09 minutes 58 seconds latitude north and 36 degree 54 minutes 13 seconds longitude east at a place called Endachi'u;

14/ thence, up to beacon number 14 at 14 degree 09 minutes 43 seconds latitude north and 36 degree 55 minutes 12 seconds longitude east around Hagereselam;

15/ thence, up to beacon number 15 at 14 degree 09 minutes 25 seconds latitude north and 36 degree 55 minutes 19 seconds longitude east at a place called Atsmi Harmaz;

16/ thence, up to beacon number 16 at 14 degree 09 minutes 38 seconds latitude north and 36 degree 56 minutes 12 seconds longitude east;

17/ thence, up to beacon number 17 at 14 degree 09 minutes 46 seconds latitude north and 36 degree 58 minutes 02 seconds longitude east;

18/ thence, up to beacon number 18 at 14 degree 09 minutes 46 seconds latitude north and 36 degree 58 minutes 14 seconds longitude east;

19/ thence, up to beacon number 19 at 14

ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ36 ዲግሪ 58 ደቂቃ 28 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አሥራ ዘጠኝ ድረስ፤

፳/ ከዚያም በ14 ዲግሪ 09 ደቂቃ 16 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ36 ዲግሪ 58 ደቂቃ 33 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሃያ ድረስ፤

፳፩/ ከዚያም ሽንተረር ሚዓም ጤል በሚባለው ቦታ ላይ በ14 ዲግሪ 07 ደቂቃ 15 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ36 ዲግሪ 58 ደቂቃ 34 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሃያ አንድ ድረስ፤

፳፪/ ከዚያም በ14 ዲግሪ 07 ደቂቃ 02 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ36 ዲግሪ 59 ደቂቃ 30 ሴኮንድ ምስራቅ እስከተመለከተው ጉልት ቁጥር ሃያ ሁለት፤

፳፫/ከዚያም ደቡብ አቅጣጫን በመከተል ሚዓምጤል ጋራ ስር በ14 ዲግሪ 06 ደቂቃ 37 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ36 ዲግሪ 59 ደቂቃ 46 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሃያ ሦስት ድረስ፤

፳፬/ ከዚያም ተመሳሳይ አቅጣጫን በመከተል በ14 ዲግሪ 05 ደቂቃ 27 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ36 ዲግሪ 59 ደቂቃ 03 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሃያ አራት ድረስ፤

፳፭/ ከዚያም ኩይሳ ዋርካ ተፋሰስ ራስጌ ላይ በ14 ዲግሪ 04 ደቂቃ 48 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 01 ደቂቃ 21 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሃያ አምስት ድረስ፤

፳፮/ ከዚያም በ14 ዲግሪ 05 ደቂቃ 46 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 01 ደቂቃ 16 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘው

degree 09 minutes 41 seconds latitude north and 36 degree 58 minutes 28 seconds longitude east;

20/ thence up to beacon number 20 at 14 degree 09 minutes 16 seconds latitude north and 36 degree 58 minutes 33 seconds longitude east;

21/ thence, up to beacon number 21 at 14 degree 07 minutes 15 seconds latitude north and 36 degree 58 minutes 34 seconds longitude east at a place called Shenterer Mi'am Tel;

22/ thence, up to beacon number 22 at 14 degree 07 minutes 02 seconds latitude north and 36 degree 59 minutes 30 seconds longitude east;

23/ thence, following the southward up to beacon number 23 at 14 degree 06 minutes 37 seconds latitude north and 36 degree 59 minutes 46 seconds longitude east at the foot of Mi'am Tel Hill;

24/ thence, following the same direction up to beacon number 24 at 14 degree 05 minutes 27 seconds latitude north and 36 degree 59 minutes 03 seconds longitude east;

25/ thence up to beacon number 25 at 14 degree 04 minutes 48 seconds latitude north and 37 degree 01 minutes 21 seconds longitude east at the watershed of Kuysa Rasge Basin;

26 / thence, up to beacon number 26 at 14 degree 05 minutes 46 seconds latitude north and 37 degree 01 minutes 16

ጉልት ቁጥር ሃያ ስድስት ድረስ፤

፳፯/ ከዚያም በ14 ዲግሪ 06 ደቂቃ 18 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 01 ደቂቃ 31 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሃያ ሰባት ድረስ፤

፳፰/ ከዚያም ውህደት ብሎክ አካባቢ በ14 ዲግሪ 06 ደቂቃ 07 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 03 ደቂቃ 42 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሃያ ስምንት ድረስ፤

፳፱/ ከዚያም በ14 ዲግሪ 06 ደቂቃ 14 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 03 ደቂቃ 52 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሃያ ዘጠኝ ድረስ፤

፴/ ከዚያም በአካባቢው ያለውን ተረተር ተከትሎ በ14 ዲግሪ 05 ደቂቃ 56 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 05 ደቂቃ 00 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሠላሳ ድረስ፤

፴፩/ ከዚያም በ14 ዲግሪ 05 ደቂቃ 02 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 08 ደቂቃ 12 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሠላሳ አንድ ድረስ፤

፴፪/ ከዚያም ማይወይኒ አካባቢ በ14 ዲግሪ 06 ደቂቃ 15 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 11 ደቂቃ 41 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሠላሳ ሁለት ድረስ፤

፴፫/ ከዚያም ማይጨው አካባቢ በ14 ዲግሪ 07 ደቂቃ 51 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 13 ደቂቃ 05 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሠላሳ ሦስት ድረስ፤

፴፬/ ከዚያም አገልግል በሚባለው ቦታ ላይ በ14 ዲግሪ 09 ደቂቃ 26 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ

seconds longitude east;

27/ thence, up to beacon number 27 at 14 degree 06 minutes 18 seconds latitude north and 37 degree 01 minutes 31 seconds longitude east;

28/ thence, up to beacon number 28 at 14 degree 06 minutes 07 seconds latitude north and 37 degree 03 minutes 42 seconds longitude east at around Wuhdet Block;

29/ thence, up to beacon number 29 at 14 degree 06 minutes 14 seconds latitude north and 37 degree 03 minutes 52 seconds longitude east;

30/ thence, following the rift in the area up to beacon number 30 at 14 degree 05 minutes 56 seconds latitude north and 37 degree 05 minutes 00 seconds longitude east;

31/ thence, up to beacon number 31 at 14 degree 05 minutes 02 seconds latitude north and 37 degree 08 minutes 12 seconds longitude east;

32/ thence, up to beacon number 32 at 14 degree 06 minutes 15 seconds latitude north and 37 degree 11 minutes 41 seconds longitude east at around Mayweyni;

33/ thence, up to beacon number 33 at 14 degree 07 minutes 51 seconds latitude north and 37 degree 13 minutes 05 seconds longitude east at around Maychew;

34/ thence, up to beacon number 34 at 14 degree 09 minutes 26 seconds latitude

እና በ37 ዲግሪ 12 ደቂቃ 44 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሠላሳ አራት ድረስ፤

፴፭/ ከዚያም መትረቢል ወንዝ አጠገብ ዲማዛፍ ጋራ ላይ በ14 ዲግሪ 09 ደቂቃ 15 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 14 ደቂቃ 24 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሠላሳ አምስት ድረስ፤

፴፮/ ከዚያም ማይ ቆለንቋል በሚባለው ቦታ ላይ በ14 ዲግሪ 11 ደቂቃ 26 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 15 ደቂቃ 55 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሠላሳ ስድስት ድረስ፤

፴፯/ ከዚያም አዲጎሹ አካባቢ በ14 ዲግሪ 12 ደቂቃ 44 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 17 ደቂቃ 22 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሠላሳ ሰባት ድረስ፤

፴፰/ ከዚያም እንግርብ በሚባለው ቦታ ላይ በ14 ዲግሪ 10 ደቂቃ 47 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 21 ደቂቃ 48 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሠላሳ ስምንት ድረስ፤

፴፱/ ከዚያም እንዳርቃይ ጋራ ጫፍ ላይ በ14 ዲግሪ 07 ደቂቃ 45 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 23 ደቂቃ 45 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ሠላሳ ዘጠኝ ድረስ፤

፵/ ከዚያም ጥቁር አፈር በሚባለው ቦታ ላይ በ14 ዲግሪ 07 ደቂቃ 35 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 25 ደቂቃ 22 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አርባ ድረስ፤

፵፩/ ከዚያም ወደ ደቡብ ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ በ14 ዲግሪ 07 ደቂቃ 30 ሴኮንድ

north and 37 degree 12 minutes 44 seconds longitude east at around Agelgil;

35/ thence, up to beacon number 35 at 14 degree 09 minutes 15 seconds latitude north and 37 degree 14 minutes 24 seconds longitude east on the hills of Dimazaf near Metrebel river;

36/ thence, up to beacon number 36 at 14 degree 11 minutes 26 seconds latitude north and 37 degree 15 minutes 55 seconds longitude east at a place called Mai Qolenqual;

37/ thence, up to beacon number 37 at 14 degree 12 minutes 44 seconds latitude north and 37 degree 17 minutes 22 seconds longitude east at around Adi Goshu;

38/ thence, up to beacon number 38 at 14 degree 10 minutes 47 seconds latitude north and 37 degree 21 minutes 48 seconds longitude east at a place called Engirib;

39/ thence, up to beacon number 39 at 14 degree 07 minutes 45 seconds latitude north and 37 degree 23 minutes 45 seconds longitude east on the top of Enda'arqay Hills;

40/ thence, up to beacon number 40 at 14 degree 07 minutes 35 seconds latitude north and 37 degree 25 minutes 22 seconds longitude east at around a place called Tiqur Afer;

41/ thence, turning to the south-eastward up to beacon number 41 at 14 degree 07

ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 25 ደቂቃ 29 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አርባ አንድ ድረስ፤

፵፪/ ከዚያም በ14 ዲግሪ 07 ደቂቃ 12 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 25 ደቂቃ 22 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አርባ ሁለት ድረስ፤

፵፫/ ከዚያም ቀልቀል ማይ ዓጋዜን በሚባለው ቦታ ላይ በ14 ዲግሪ 06 ደቂቃ 47 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 29 ደቂቃ 17 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አርባ ሦስት ድረስ፤

፵፬/ ከዚያም እንደቦ በሚባለው ቦታ ላይ በ14 ዲግሪ 05 ደቂቃ 56 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 29 ደቂቃ 35 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አርባ አራት ድረስ፤

፵፭/ ከዚያም ሙሟት ቡላ እንደርቃይ አካባቢ በ14 ዲግሪ 03 ደቂቃ 33 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 31 ደቂቃ 26 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አርባ አምስት ድረስ፤

፵፮/ ከዚያም በሰሜን አቅጣጫ ተከዜ ወንዝን ተከትሎ ከሱር ወንዝ ጋር በሚገናኙበት ቦታ ላይ በ14 ዲግሪ 05 ደቂቃ 11 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 39 ደቂቃ 25 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አርባ ስድስት ድረስ፤

፵፯/ ከዚያም በ14 ዲግሪ 06 ደቂቃ 03 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 40 ደቂቃ 15 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አርባ ሰባት ድረስ፤

፵፰/ ከዚያም በእንዳጉሬዛ ላይኛው ጫፍ እንደዝባ አጠገብ በ14 ዲግሪ 07 ደቂቃ 17 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 40 ደቂቃ 29

minutes 30 seconds latitude north and 37 degree 25 minutes 29 seconds longitude east;

42/ thence, up to beacon number 42 at 14 degree 07 minutes 12 seconds latitude north and 37 degree 25 minutes 22 seconds longitude east;

43/ thence, up to beacon number 43 at 14 degree 06 minutes 47 seconds latitude north and 37 degree 29 minutes 17 seconds longitude east at a place called Kelkel Mai Agazen;

44/ thence, up to beacon number 44 at 14 degree 05 minutes 56 seconds latitude north and 37 degree 29 minutes 35 seconds longitude east at a place called Endebo;

45/ thence, up to beacon number 45 at 14 degree 03 minutes 33 seconds latitude north and 37 degree 31 minutes 26 seconds longitude east at around Mumuat Bula Enda'ạrqay;

46/ thence, following Tekeze river at the confluence with Sur river up to beacon number 46 at 14 degree 05 minutes 11 seconds latitude north and 37 degree 39 minutes 25 seconds longitude east;

47/ thence, up to beacon number 47 at 14 degree 06 minutes 03 seconds latitude north and 37 degree 40 minutes 15 seconds longitude east;

48/ thence, up to beacon number 48 at 14 degree 07 minutes 17 seconds latitude north and 37 degree 40 minutes 29

ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አርባ ስምንት ድረስ፤

፵፱/ ከዚያም ዓድዋ ወንዝ ካምፕ አጠገብ በ14 ዲግሪ 09 ደቂቃ 55 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 39 ደቂቃ 23 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አርባ ዘጠኝ ድረስ፤

፶/ ከዚያም እንደርቃ ተራራ ላይ በ14 ዲግሪ 09 ደቂቃ 46 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 37 ደቂቃ 59 ሴኮንድ ምሥራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አምሳ ድረስ፤

፶፩/ ከዚያም ምቅልቃል እንዳ ገብረሳሙኤል በሚባለው ቦታ ላይ በ14 ዲግሪ 08 ደቂቃ 52 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 36 ደቂቃ 03 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አምሳ አንድ ድረስ፤

፶፪/ ከዚያም አትካሮ በሚባለው ቦታ ላይ በ14 ዲግሪ 08 ደቂቃ 52 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 35 ደቂቃ 01 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አምሳ ሁለት ድረስ፤

፶፫/ ከዚያም በ14 ዲግሪ 09 ደቂቃ 38 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 33 ደቂቃ 31 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አምሳ ሦስት ድረስ፤

፶፬/ ከዚያም ዝባን ማይ መፃዕ በሚባለው ቦታ ላይ በ14 ዲግሪ 10 ደቂቃ 31 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 33 ደቂቃ 03 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አምሳ አራት ድረስ፤

፶፭/ ከዚያም ጨረር ቦዘይ በሚባለው ቦታ በ14 ዲግሪ 12 ደቂቃ 57 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ

seconds longitude east on the upper top of Endagureza near Endeziba;

49/ thence, up to beacon number 49 at 14 degree 09 minutes 55 seconds latitude north and 37 degree 39 minutes 23 seconds longitude east near Adwa river Camp;

50/ thence, up to beacon number 50 at 14 degree 09 minutes 46 seconds latitude north and 37 degree 37 minutes 59 seconds longitude east on top of Enderqa Mountain;

51/ thence, up to beacon number 51 at 14 degree 08 minutes 52 seconds latitude north and 37 degree 36 minutes 03 seconds longitude east at a place called Miqilqal Enda Gebre Samuel;

52/ thence, up to beacon number 52 at 14 degree 08 minutes 52 seconds latitude north and 37 degree 35 minutes 01 seconds longitude east at a place called Atkaro;

53/ thence, up to beacon number 53 at 14 degree 09 minutes 38 seconds l[illegible] 8008 north and 37 degree 33 minutes 31 seconds longitude east;

54/ thence, up to beacon number 54 at 14 degree 10 minutes 31 seconds latitude north and 37 degree 33 minutes 03 seconds longitude east at a place called Ziban Mai Metsa'e;

55/ thence, up to beacon number 55 at 14 degree 12 minutes 57 seconds latitude

እና በ37 ዲግሪ 32 ደቂቃ 39 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አምሳ አምስት ድረስ፤

፶፮/ ከዚያም ጅጉሪ በሚባለው ቦታ ላይ በ14 ዲግሪ 15 ደቂቃ 22 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 33 ደቂቃ 01 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አምሳ ስድስት ድረስ፤

፶፯/ ከዚያም በ14 ዲግሪ 18 ደቂቃ 00 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 32 ደቂቃ 50 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አምሳ ሰባት ድረስ፤

፶፰/ ከዚያም ፀቢብ በሚባለው ቦታ ላይ በ14 ዲግሪ 20 ደቂቃ 22 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 31 ደቂቃ 03 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አምሳ ስምንት ድረስ፤

፶፱/ ከዚያም በ14 ዲግሪ 21 ደቂቃ 55 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 27 ደቂቃ 35 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር አምሳ ዘጠኝ ድረስ፤

፷/ ከዚያም ትክል ድንጋይ በሚባለው ቦታ ላይ በ14 ዲግሪ 24 ደቂቃ 22 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 26 ደቂቃ 14 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ስልሳ ድረስ፤

፷፩/ ከዚያም ታሒታይ ሙራጉዞ በሚባለው ቦታ ላይ በ14 ዲግሪ 25 ደቂቃ 15 ሴኮንድ ሰሜን ላቲቲዩድ እና በ37 ዲግሪ 25 ደቂቃ 28 ሴኮንድ ምስራቅ ሎንጊቲዩድ እስከሚገኘው ጉልት ቁጥር ስልሳ አንድ ድረስ፤

፷፪/ ከዚያም ወደ ሰሜን አቅጣጫ በመጓዝ ጉልጉላ ወንዝን ተከትሎ ከተከዜ ወንዝ ጋር

north and 37 degree 32 minutes 39 seconds longitude east at place called Terer Bozey;

56/ thence, up to beacon number 56 at 14 degree 15 minutes 22 seconds latitude north and 37 degree 33 minutes 01 seconds longitude east at a place called Jiguri;

57/ thence, up to beacon number 57 at 14 degree 18 minutes 00 seconds latitude north and 37 degree 32 minutes 50 seconds longitude east;

58/ thence, up to beacon number 58 at 14 degree 20 minutes 22 seconds latitude north and 37 degree 31 minutes 03 seconds longitude east at a place called Tsebib;

59/ thence, up to beacon number 59 at 14 degree 21 minutes 55 seconds latitude north and 37 degree 27 minutes 35 seconds longitude east;

60/ thence, up to beacon number 60 at 14 degree 24 minutes 22 seconds latitude north and 37 degree 26 m 8009 [illegible] seconds longitude east at a place called Tikil Dingay;

61/ thence, up to beacon number 61 at 14 degree 25 minutes 15 seconds latitude north and 37 degree 25 minutes 28 seconds longitude east at a place called Tahitay Muraguzo;

62/ thence, heading in the northern direction to Gulgula river at a place where it joins

በመገናኘት፣ የተከዜ ወንዝን ተከትሎ በሕለጊን ሰሜናዊ ጫፍ ካለው ጉልት ቁጥር አንድ ጋር ይገጥማል::

**፭. <u>የፓርኩ አስተዳደር</u>**

፩/ ባለሥልጣኑ በአዋጅ ቁጥር ፭፻፸፭/፪ሺ አንቀጽ ፬ መሠረት ቃፍታ ሁመራ ወረዳ ውስጥ በሚያደራጀው የፓርኩ ጽሕፈት ቤት አማካኝነት ፓርኩን ያለማል፣ ያስተዳድራል፣ ሕገ ወጥ ተግባራት እንዳይፈጸሙበት ይከላከላል::

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የፓርኩ አማካሪ ኮሚቴ (ከዚህ በኋላ "ኮሚቴ" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ ደንብ ተቋቁሟል::

**፮. <u>የኮሚቴ አባላት</u>**

ኮሚቴው የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፤

፩/ የፓርኩ አዋሳኝ ወረዳ ዋና አስተዳዳሪዎች (በየዓመቱ በመቀያየር)........,.........ሰብሳቢ፤

፪/ የፓርኩ አዋሳኝ ወረዳ ዋና አስተዳዳሪዎች (በየዓመቱ በመቀያየር.................አባላት፤

፫/ የፓርኩ አዋሳኝ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽህፈት ቤት ኃላፊዎች ተወካዮች.,...አባላት፤

፬/ ፓርኩ አዋሳኝ ቀበሌ አስተዳደር ኃላፊዎች.............................አባላት፤

፭/ የፓርኩ አዋሳኝ ቀበሌዎች ሴቶችና ወጣቶች ማህበራት ሁለት ተወካዮች.......አባላት፤

፮/ ለፓርኩ ጐብኚዎች አገልግሎት የሚሠጡ የቱሪስት ተቋማት አንድ ተወካይ.........አባል፤

፯/ የፓርኩ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ...አባልና ፀሐፊ

with Tekeze river; and following the Tekeze river basin and then joins with initial beacon number 1 at the northern tip.

**5. <u>Administration of the Park</u>**

1/ The Authority shall develop, administer and prevent the Park from illegal acts through the Park's office to be organized in Qafta Humera pursuant to Article 4 of the Proclamation No. 575/2008.

2/ Without prejudice to sub-article (1) of this Article, the Park's Advisory Committee (hereinafter called the "Committee") is hereby established.

**6. <u>Members of the Committee</u>**

The Committee shall have the following members:

1/chief administrators of the Park's neighboring Woredas (annually in rotation... Chairperson

2/chief administrators of the Park's neighboring woredas (annually in rotation)... ...members

3/ representatives of heads of Culture and Tourism Offices of the Park's neighboring woredas..............................members

4/ heads of the Park's neighboring Kebele administrations .....................members

5/ two representative from Youth and Women Associations of neighboring kebele.. ..........................................members

6/ a representative of tour operator ...... ..............................member

7/ head of the office of the Park ...... member and secretary

፯. የኮሚቴው ሥልጣንና ተግባራት

ኮሚቴው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

፩/ የፓርኩ ጽሕፈት ቤት የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት እንዲወጣ ምክር ይሰጣል፤

፪/ በፓርኩ አካባቢ የሚኖሩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ባለቤትነት ተሰምቷቸው በፓርኩ አጠባበቅ ላይ የጎላ ተሳትፎ እንዲኖራቸው የሚያስችሉ ሃሳቦችን ያቀርባል፤

፫/ ከፓርኩ ጽሕፈት ቤት ጋር በመሆን የፓርኩን ዓመታዊ እቅድ ያወጣል፤ የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ለባለሥልጣኑ ከመቅረቡ በፊት ገምግሞ አስተያየት ይሰጣል።

፰. የኮሚቴው ስብሰባ

፩/ ኮሚቴው በየሦስት ወሩ ይሰበሰባል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማንኛውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል።

፪/ ከኮሚቴው አባላት ከግማሽ በላይ በስብሰባ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል።

፫/ የኮሚቴው የውሳኔ ሀሳብ በድምጽ ብልጫ ያልፋል፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።

፬/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ኮሚቴው የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

7. Powers and Duties the Committee

The Committee shall have the powers and duties to:

1/ advice the office of the Park in carrying out its duties and responsibilities;

2/ advise the office of the Park to enhance the contribution of the local community around the Park in the management and conservation of the Park with a sense of ownership;

3/ prepare annual plans of the Park together with the office of the park and, evaluate and review performance reports before they are being submitted to the Authority.

8. Meetings of the Committee

1/ The Committee shall meet once in every three months; provided, however, that extra-ordinary meetings of the Committee may be held at any time, as may be necessary.

2/ There shall be quorum where more than half of the members of the Committee are present at a meeting.

3/ Recommendations of the Committee shall be passed by majority votes; in case of a tie the Chairperson shall have a casting vote.

4/ Without prejudice to the provisions of this Article, the Committee may adopt its own rules of procedure for conducting meetings.

፱/ **የተከለከሉ ተግባራት**

በዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፷፫/፪ሺ፩ አንቀጽ ፭(፩) ከተመለከቱት የተከለከሉ ተግባራት በተጨማሪ የሚከተሉትን ተግባራት በፓርኩ ክልል ውስጥ መፈፀም የተከለከለ ነው፤

፩/ መርዛማ ንጥረ ነገሮችን ይዞ ወደ ፓርኩ ውስጥ መግባት፤

፪/ ለምግብ መያዣናለመሳሰሉት የተጠቀሙባቸውን ቆሻሻዎች በዘፈቀደ በየቦታው በፓርኩ ውስጥ መጣል፤

፫/ የእንስሳት ማጥመጃ ወይም ማደኛ መሣሪያ ይዞ ወደ ፓርኩ ውስጥ መግባት።

፲. **አስተዳደራዊ ቅጣት**

፩/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፱ ወይም በዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፷፫/፪ሺ፩ አንቀጽ ፭(፩) የተከለከሉትን ተግባራት በመተላለፍ በዱር እንስሳት ወይም በዱር እንስሳት ሀብት ላይ ጉዳት ያደረሰ ማንኛውም ሰው በአዋጁ አንቀጽ ፲፮ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ለ) መሠረት መቀጣቱ እንደተጠበቀ ሆኖ በዱር እንስሳት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፷፫/፪ሺ፩ ላይ በተቀመጠው የዋጋ ተመን መሠረት የዱር እንስሳውን ወይም የዱር እንስሳት ሀብቱን ዋጋ ይከፍላል።

፪/ባለሥልጣኑ በፓርኩ ከሚገኝበት አካባቢ አስተዳደር ጋር በመነጋገር ወደ ፓርኩ ክልል

9. **Prohibited Activities**

In addition to the prohibited activities provided for under Article 5(1) of the Wildlife Development, Conservation and Utilization Council of Ministers Regulations No. 163/2008, carrying out the following activities within the Park area shall also be prohibited:

1/ entering the Park holding poisonous substances;

2/ arbitrary disposal of trash in the Park such as packing cases of foodstuff and other leftovers;

3/ entering the Park with a snare or a hunting weapon.

10. **Administrative Penalty**

1/ Whosoever causes damage to wildlife or wildlife resource in contravention of Article 9 of these Regulations or sub-article (1) of Article 5 of the Wildlife Development, Conservation and Utilization Council of Ministers Regulation No. 163/2008 shall, without prejudice to the penalty prescribed under paragraph (b) of sub-artic Article 16 of the Proclamation, be liable to pay the price of the wildlife or wildlife resource as provided for by the Wildlife Development, Conservation and Utilization Council of Ministers Regulation No. 163/2008.

2/ The Authority may, in consultation with the local administrations adjoining the

የሚገቡ የቤት እንስሳትን በሚመለከት የሚጣል ከአካባቢው ነዋሪዎች አቅም ጋር ተመጣጣኝ የሆነ አስተዳደራዊ መቀጮ ተመን ሊያወጣ ይችላል፡፡

፲፩. <u>**የመተባበር ግዴታ**</u>

ማንኛውም ሰው ይህን ደንብ በማስፈጸም ረገድ ከባለሥልጣኑ ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

፲፪. <u>**ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**</u>

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ጥር ፲፪ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም

ኃይለማርያም ደሳለኝ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ

ጠቅላይ ሚኒስትር



Park, determine the rate of fine to be imposed for the transgression of domestic animals into the Park, by taking into account the financial capacity of the local communities.

11. <u>**Duty to Cooperate**</u>

Any person shall have duty to cooperate with Authority for the implementation of this Regulation.

12. <u>**Effective Date**</u>

This Regulation shall enter into force on the date of publication in Federal Negarit Gazette.

Done at Addis Ababa, this 20th day of January, 2015.


**HAILEMARIAM DESSALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC**

**REPUBLIC OF ETHIOPIA**

# አባሪ / Annex

## የቃፍታ ሽራሮ ብሔራዊ ፓርክ ካርታ/ Qafta-Sheraro National Park Map



ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት